AMHARIC

Commonwealth Ombudsman

**የኮመንዌልዝ ኦምብድስማን ከአውስትራሊያ የመንግስት መሥሪያ ቤቶች ላይ የሚቀርበውን አቤቱታ የሚመረምር ከማንም ተፅእኖ ነፃ የሆነ ግለሰብ ነው።**

## የኦምብድስማኑ ተግባር

ኦምብድስማኑ ከብዙዎቹ የአውስትራሊያ የመንግስት ደርጅቶች ላይ የሚቀርቡትን አቤቱታዎች መመርመር ይችላል። እነዚህም የመንግስት ድርጅቶች የሚከተሉትን ይጨምራሉ። ሴንተርሊንክ፥ ታክስ ጽ/ቤት፥ የልጆች እንክብካቤ ድጋፍ ሰጪ ድርጅት፥ የኢሚግሬሽን ጽ/ቤትና የአውስትራሊያ ፓስታ ቤት።

ማንኛውም ተግባር ወይም ውሳኔ ትክክለኛ አለመሆኑን፥ እንዲሁ ዝም ብሎ በችኮላ የተወሰደ መሆኑን ወይም አድሎአዊ መሆኑን የሚወስነው ኦምብድስማኑ ነው። ከዚህም በተጨማሪ የአስተዳደር ውሳኔ ያልተደረገባቸው ወይም ውሳኔ ሳይደረግባቸው የዘገዩ ጉዳዮችን የሚመረምር አካል ነው።

በሌላ በኩል ግን ኦምብድስማኑ የግል ሰዎችን ወይም ኩባንያዎችን፥ የህግ ውሳኔዎችን በክፍለሃገሮች ወይም በአካባቢ መንግስት፥ በመንግስት ሚኒስትሮች ወይም በተወሰኑ የመንግስት የንግድ ድርጅቶች የወጡ ህጎችን ወይም ውሳኔዎችን የሚመለከቱ አቤቱታዎችን መመርመር አይችልም።

ኦምብድስማኑ ገለልተኛ ነው በተጨማሪም ትክክለኛና አድሎ የሌለበት ውጤትን ለማምጣት ነው የሚሰራው።

ኦምብድስማኑ የመንግስት የአስተዳደር አሰራር እንዲሻሻል በዚህም በአስተዳደር አሰራር የሚፈጠሩ ችግሮች እንዳይደጋገሙ ለመከላከል ይሰራል።

## የኦምብድስማኑ ስልጣኖች

ኦምብድስማኑ አቤቱታዎችን ለመመርመር ብዙ ስልጣኖች አሉት። እነዚህም ስልጣኖች የመንግስት ሰራተኞች ሰነዶችን እንዲያስረክቡ ወይም ለሚቀርቡላቸው ጥያቄዎች መልስ እንዲሰጡ ማድረግን ይጨምራል።

ኦምብድስማኑ በመንግስት አስተዳደር ላይ ስህተትን ካገኘ የሚመለከተው ወኪል ድርጅት ይሄንን ስህተት እንዲያስተካክል ማሳሰብ ወይም ለስህተቱ መፍትሄ ማቅረብ ይችላል።

ለምሳሌ ስህተት የተገኘበት የመንግስት ወኪል ድርጅት ማብራሪያ እንዲሰጥ ወይም ይቅርታ እንዲጠይቅ፥ ውሳኔን እንዲቀበል ወይም እንዲያስተካክል፥ ዕዳን ይቅር የማለት ወይም ካሳ እንዲከፈል ማዘዝ ይችላል።

## አቤቱታ እንዴት ነው የሚያቀርቡት

የኦምብድስማኑን ቢሮ ከማነጋገርዎ በፊት አቤቱታዎን የሚያቀርቡበትን የመንግስት ድርጅት አስተዳደር ክፍል በተለይም አቤቱታን የሚቀበለውን ክፍል፥ የዚህ አይነት ክፍል ካለ በዚህ ድርጅት ውስጥ ስለ አቤቱታዎ በማነጋገር ችግሩን ለመፍታት ይሞክሩ። አቤቱታዎ ውሳኔን የሚመለከት ከሆነ በመጀመሪያ የሚቻል ከሆነ ውሳኔው እንደገና እንዲታይልዎት ይጠይቁ።


local call charge COMPLAINTS 1300 362 072
email ombudsman@ombudsman.gov.au | web www.ombudsman.gov.au


Commonwealth OMBUDSMAN

ኦምብድስማኑ በሁሉም ክፍለሃገሮችና ልዩ አስተዳደሮች ዋና ዋና ከተሞች ውስጥ ቢሮዎች አሉት።  አቤቱታዎን ቢሮ ድረስ መጥተው ማቅረብ ይችላሉ ወይም በስልክ፥ በደብዳቤ፥ በፋክስ ወይም በኢሜይል ማቅረብ ይችላሉ ።

በከተማ ውስጥ የስልክ ጥሪ ዋጋ የኦምብድስማኑን ቢሮ በስልክ ቁጥር 1300 362 072 ደውለው ማነጋገር ይችላሉ ።

ሌላ ሰው እንደ ጓደኛ፥ ዘመድ ወይም የማህበረሰብ ሠራተኛ እርስዎን ወክሎ አቤቱታዎን እንዲያቀርብልዎት ማድረግም ይችላሉ።

ቋንቋቸው እንግሊዝኛ ካልሆነ አገሮች የመጡ ሰዎች ከፈለጉ በ131 450 በመደወል በትርጉም አገልግሎት ክፍል (ቲስ) በኩል የኦምብድስማኑን ቢሮ ማነጋገር ይችላሉ ወይም በራሳቸው ቋንቋ በፁሁፍ አቤቱታቸውን ማስገባት ይችላሉ።

## ሚስጥራዊና ነፃ አገልግሎት

አቤቱታን መመርመር በሚስጢር የሚጠበቅ ሲሆን ይህም አገልግሎት ነፃ ነው።

# አቤቱታን ለማቅረብ መብት አልዎት

ይህ መረጃ እንደ መመሪያ ብቻ እንዲሆንዎ ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ለበለጠ መረጃ የኮመንዌልዝን ኦምብድስማን ያነጋግሩ።

## ይደውሉልን

በከተማ የስልክ ጥሪ ዋጋ አጠገብዎ የሚገኘውን የኦምብድስማን ቢሮ ማነጋገር ይችላሉ። ለዚህም በሚከተሉት ቁጥሮች ይደውሉ።

**ብሔራዊ አቤቱታ ማቅረቢያ መሥመር - 1300 362 072**
(በሞባይል የሚደውሉ ከሆነ ግን የሚከፍሉት ያው በሞባይል ዋጋ ነው)

Email ombudsman@ombudsman.gov.au
Web   www.ombudsman.gov.au

## የኮመንዌልዝ ኦምብድስማን ቢሮዎች

**ADELAIDE**
Tel 1300 362 072
Fax 08 8226 8618
Level 5, 50 Grenfell Street
Adelaide SA 5000

**BRISBANE**
Tel 1300 362 072
Fax 07 3229 4010
Level 17, 53 Albert Street
Brisbane QLD 4000

**CANBERRA & NATIONAL OFFICE**
Tel 1300 362 072
Fax 02 6249 7829
GPO Box 442
Canberra ACT 2601

Ground Floor, 1 Farrell Place
Canberra City ACT 2600

**DARWIN**
Tel 1300 362 072
Fax 08 8941 5400
GPO BOX 1344, Darwin NT 0801

Level 12, NT House
Cnr Bennett & Mitchell Streets
Darwin NT 0801

**HOBART**
Tel 1300 362 072
Fax 03 6233 8966
GPO Box 960
Hobart Tas 7001

Ground Floor
99 Bathurst Street
Hobart TAS 7000

**MELBOURNE**
Tel 1300 362 072
Fax 03 9867 3750
Level 1
441 St Kilda Road
Melbourne VIC 3004

**PERTH**
Tel 1300 362 072
Fax 08 9221 4381
PO Box Z5386
St Georges Terrace
Perth WA 6831
Level 12, St Martin's Tower
44 St Georges Terrace
Perth WA 6000

**SYDNEY**
Tel 1300 362 072
Fax 02 9211 4402
PO Box K825
Haymarket NSW 1240

Level 7, North Wing
Sydney Central
477 Pitt Street
Sydney NSW 2000

## አቤቱታዎን ማቅረብ እንዲችሉ የሚረዱ አገልግሎቶች

እንግሊዝኛን በደንብ መናገር የሚያስቸግርዎት ከሆነ በ 131 450 ትርጉም አገልግሎት (ቲስ) ይደውሉ። ልንረዳዎ እንችላለን።

የመስማት፥ የማየት ወይም የመናገር ችግር ካለብዎት የቲቲዋይ አገልግሎት በመልእክት ማሰራጫ አገልግሎት (National Relay Service) በ133 677 በኩል ይደውሉ።